# የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሰራተኞች የአካባቢ ጥበቃ ቀንን አከበሩ

በዓለም ለ42ኛ በአገራችን ለ21ኛ ጊዜ የሚከበረዉ የአካባቢ ቀን በቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢኒስቲትዩት በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ተከበረ፡፡

በዓሉን አስመልክቶ በኢኒስቲትዩቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ በተካሄደዉ የዉይይት መድረክ ላይ የኢኒስቲትዩቱ የሰዉ ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ወንድሙ ኩመራ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንዳሉት አካባቢ ህይወት ያላቸውን ማለትም፣ ሰውን እንስሳትና እጽዋትን እና ህይወት የሌላቸውን ከባቢ አየር፣ የፀሐይ ብርሀን፣ ማዕድን እና ሌሎችንም የሚያካትት ሲሆን እነዚህ ክፍሎች እርስ በርሳቸው ቁርኝት መስተጋብር የሚወሰን ነው፡፡





በአካባቢ ላይ የሚደርስ መዛባት የሚመጣው ጉዳት ከፍተኛ ስለሆነ ለእንደኛ ዓይነት ግብርና ተኮር የኑሮ ዋስትና ያለው ህዝብ እና ብዙ ለኢንዱስትሪዎቻችን ግብዓቶች የሚሆኑ እንደ ቆዳና ሌጦ ከግብርናው ዘርፍ የሚገኙ በመሆናቸው ሁላችንም የአካባቢ እንክብካቤ ስራ ላይ በእኔነት መሳተፍን እና መጠበቅ ይገባናል ብለዋል ዳይሬክተሩ በንግግራቸዉ፡፡

ዘንድሮ **"በየዓመቱ በሁሉም ቦታ ሁላችንም ለተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና ለአከባቢ ጥበቃ ስራዎች በጋራ እንነሳ!!** በሚል መሪ ቃል በተከበረዉ በዓል ላይ አካባቢ ጥበቃን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፍ በአቶ አንተነህ ሙህዬ ቀርቦ ዉይይት ተካሂዶበታል፡፡

ከዉይይቱ በኋላም የኢኒስቲትዩቱ ሰራተኞች ሀገር በቀል እፅዋትን በኢኒስቲትዩቱ ቅጥር ግቢ ተክለዋል፡፡



